# ከአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ የተሰጠ መግለጫ፣

## የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ ብሔራዊ ምክር ቤት ተከታታይ ስብሰባዎችን በማድረግ ዐበይት ውሳኔዎችን አሳለፈ፣

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በ2002 ዓ.ም ሐገራዊ ምርጫ ማግስት ባደረጋቸው ተከታታይ ስብሰባዎች የምርጫውን የተሟላ ግምገማ በፓርቱው የጥናትና ምርምር ቋሚ ኮሜቴ፤ የፓርቲውን የወደፊት አቅጣጫና ስትራቴጂ በሚመለከት በፓርቲው የዕቅድና ስትራቴጂ ቋሚ ኮሚቴ እና እንዲሁም የፓርቲውን የ2002 ዓ.ም ዕቅድና በጀት አፈፃፀም ሪፓርት በድርጅቱ ም/ሊ መንበር እንዲዘጋጅ መወሰኑንና ይኸውም በመከናወን ላይ መሆኑን በሰኔ ወር ለተጠራው የብሔራዊ ም/ቤት ስብሰባ ሪፖርት አቅርቦ ነበር፡፡ ምክር ቤቱም ይህንኑ ሃሳብ በመውሰድ ስራዎቹ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ በተለይም ደግሞ በዕቅድና ስትራተጂ ቋሚ ኮሚቴ ለሚሰራው ስራ ተጨማሪ የሰው ሃይል ከምክር ቤቱ አባላት እንዲጨመሩ በማድረግ እና ሪፓርቶቹ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተጠናቀው እንዲቀርቡለት በወሰነው መሠረት ሐምሌ 10 ቀን 2002 ዓ.ም የጥናቶቹ ውጤቶች ተጠናቀው ለም/ቤቱ ቀርበዋል፡፡

በጥናትና ምርምር ቋሚ ኮሚቴ የምርጫ 2002 ዓ.ም ዝግጅት ግምገማን አስመልክቶ የቀረበው ጥናት ኢህአዴግ ከምርጫ 97 ማግስት ጀምሮ ለአለፉት አምስት ዓመታት የወሰዳቸውን እርምጃዎች በሰፊው ዳስሷል፡፡ በዚህም መሠረት ኢህአዴግ በአንድ በኩል ከራሱና እርሱ ከሚመራው መንግስት ወጪ ያሉትን ተቋማት የማሽመድመድ ዘመቻ ሲያካሂድ በሌላ በኩል ደግሞ የገዛ ራሱን ዓቅም ለማፈርጠም በመንግስታዊ ተቋማት ላይ ያለውን ቁጥጥር ፍፁም ለማድረግ የወሰዳቸውን እርምጃዎች ዳሷል፡፡ ኢህአዴግ በአለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ የአባላቱን ብዛት ከ500 % በላይ በማሳደግ አምስት ሚልዬን እንዳደረሰው ፤ ከእነዚህም ውስጥ ሶስት ሚልዬን ተኩል የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤት አባላት እንደሆኑ፤ በቻይና ለምርጫ መምረጥ ከሚችሉት ቻይናውያን መካከል ከአስራ ሁለቱ አንዱ የኮሚኒስት ፓርቲው አባል ሲሆን፣ ኢህአዴግ በዚህ አምስት ዓመት ሰራው ባለው ስራ ብቻ የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲን በመቅደም ለመምረጥ ዕድሜያአቸው ከደረሰ ከአስር ኢትዮጵያውያን አንዱን አባሉ ለማድረግ መቻሉን ጥናቱ አመልክቷል፡፡ አባላትን የማፍራት ዘመቻው የዜጎችን መብት እና ሰብአዊ ክብር በአስጠበቀ መልኩ ቢሆን ኖሮ አበጀህ በተባለለት ነበር፡፡ ነገር ግን ዜጐችን በጥቅማ ጥቅም በመደለልና የኑሮ ዋስትናቸውን አደጋ ላይ በመጣል የተካሄደ በመሆኑ እጅግ አስከፊ ያደርገዋል፡፡

የአንድን ፓርቲ ፈፁማዊ ቁጥጥር ለማረጋገጥ ሲባል ኢህአዴግ አፋኝ አዋጆቹን እንዳወጣ፤ የመንግስት ተቋማትን ከሕግና ከስነ ምግባር ውጪ በሆነ መንገድ እንደተጠቀመ፣ የውጭ ዕርዳታንና የሃገር ሃብትን ገደብ በሌለው መልኩ መጠቀሙንና በማንኛውም እንቅስቃሴው ራሱን ከሕግና ስነ-ሰርዓት በላይ ማስቀመጡን ጥናቱ አመልክቷል፡፡ ኢህአዴግ አስቀድሞ በወሰዳቸው አፋኝና ሕገ-ወጥ እርምጃዎች የፖለቲካ ስነ ምህዳሩንና የምርጫ ስርዓቱን የራሱን #አሸናፊነት$ እና ዘላለማዊነት ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ ሲያመቻች መቆየቱን ጥናቱ አሳይታል፡፡

ፓርቲያችን አንድነት ወደ ምርጫው የገባበት አፈና የነገሰበት ፓለቲካዊ ምሕዳር የሚፈጥረው ተፅህኖ እንደተጠበቀ ሆኖ በፓርቲው በኩል ከዚህ የላቀ ዝግጅት ማድረግ ተገቢ እንደነበር ጥናቱ ጠቁሟል፡፡ የፓርቲው ውስጣዊ ሁኔታና ለምርጫው ያደረገው ዝግጅት ከሚጠበቀው በታች እንደሆነ በጥናቱ ተመልክቷል፡፡ መድረክን የመሰረቱት ፓርቲዎች በጋራ ኘሮግራምና በጋራ ምልክት የጋራ ዕጩ ለማቅረብና በተቀናጀ አቅም የምርጫ ዘመቻውን ለማካሄድ መወሰናቸውን ተከትሎ ከዚህ ጋር የተያያዙትን ሥራዎች ለመቋጨት ሰፊ ጊዜ መወሰዱንና በዚህም ምክንያት ብዙ ስራዎች በመጨረሻዎቹ ሳምንታት መደራረባቸው፤ ጥናቱ አክሎ እንዳመለከተው ፓርቲው የውስጣዊ አቅሙን ከማጐልበት አኳያ በተለይም ደግሞ በየደረጃው ጠንካራ አመራር ለመፍጠር አብክሮ መንቀሳቀስ እንዳለበት ፣ እንዲሁም ፓርቲው በሰው ሃይል በይዘትና በብዛት ተጠናክሮ መውጣት እንደሚገባው እና በገንዘብ አቅምም በተሻለ ደረጃ አቅሙን የማጐልበት ሥራ ሊሰራ እንደሚገባው ጥናቱ አመላክቷል፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ መድረክ በኢትዮጵያ ፖለቲካ እንደ አንድ ሁነኛ ስብስብ መፈጠሩና ፓርቲያችን መድረክን መቀላቀሉ ለኢትዮጵያ ፓለቲካ አንድ ተስፋ እንደፈነጠቀ በጥናቱ ተመልክቷል፡፡ መድረክ በተመሠረተ አጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ ማግኘቱ፣ በአገሪቱ ትልቁ ተፎካካሪ ሆኖ መውጣቱና አንድነት ለዚህ ስኬት የራሱን ድርሻ መወጣቱ የሚያስመሰግን መሆኑን ጥናቱ አሳይታል፡፡ አንድነት በዚህ የምርጫ ሂደት በማለፉና በመሳተፉ ምክንያት ለወደፊት ትግሉ በርካታ ጠቃሚ ተሞክሮዎች ለማግኘት መቻሉ፤ በዚህ ሂደትም ብቃቱንና ጥራቱን ለማሳደግ እድል ከማግኘቱም ባሻገር በርካታ አዳዲስ አባላትን ለማፍራት መቻሉም ተመልክቷል፡፡ ጥናቱ አክሎ እንዳመለከተው ፓርቲው በወጣቶችና በሴቶች የተሰራው ስራ ድክመት

እንዳለበትና ሊሻሻል እንደሚገባው ተጠቁሟል፡፡ ይህም ሆኖ ግን የፓርቲያችን ወጣቶች በምርጫ ያደረጉት አስተዋጽኦ የሚያኮራ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በዕቅድና ስትራተጂ ቋሚ ኮሚቴ በኩል በቀረበው ሪፓርት ውስጥ በተለያየ ደረጃ ያሉትን አካላትና አባላት፤ በውጪ አገር ያሉ የፓርቲው የድጋፍ ኮሚቴዎች፣ ምሁራን፤ ጋዜጠኞችንና ዲፕሎማቲክ ኮር አባላት ጋር በተደረገ ውይይትና ዳሰሳዊ ጥናት የተገኘው ጥቆማ ላይ በመመርኮዝ የተዘጋጀ ሲሆን፤ በፓርቲው መርሆዎችና ኘሮግራም፤ በፓርቲው ሕገ–ደንብ እንደዚሁም ፓርቲው ለወደፊት ትኩረት ሊሰጣቸው በሚገባ ጉዳዮች ላይ አስተያየት አሰባስቦአል፡፡ ምክር ቤት የዚህ ጥናት ግኝቶች በጥናትና ምርምር ቋሚ ኮሚቴ ከቀረቡት የጥናት ውጤቶች ጋር ተዘማጅነትና ልዩነቶች እንዳሏቸው ተገንዝቧል፡፡ በተለይም ደግሞ ፓርቲው በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት እንደ ግብ ጥሎ ሊሰራባቸው በሚገባ ጉዳዮች ላይ ጠቃሚ ሃሳቦች ተጠቁሟል፡፡

ምክር ቤቱ የ2002 ዓ.ም ዕቅድና በጀት አፈፃፀም ሪፓርትም ቀርቦለት ተወያይቶበታል፡፡ በዚህ ሪፖርት ውስጥ የሊቀ መንበር ብርቱካን መታሰር፤ ብርቱካን ትፈታ በሚል የተካሄዱት ኘሮግራሞችና እንቅስቃሴዎች፤ አንድነት እንደ መድረክ አባል ያከናወናቸው ስራዎች፤ የተጓደሉ የምክር አባላትን ለመተካት የተካሄደው ኮንፈረንስና ይህን ተከትሎ የተደረጉት የሰው ሃይል ድልድል፤ በጀትና ክንውን የመሳሰሉት አንኳር ጉዳዮች በሪፓርቱ ተዳስሰዋል፡፡ ሪፓርቱ በመጨረሻም በሚዘጋጀው የወደፊት መርሃ ግብርና ዕቅድ ትኩረት የሚሹ ፓርቲው ያሉበት ተግዳሮቶችን አመልክቷል፡፡

በእነዚህ ሪፓርቶች ላይ ጥልቅ ውይይት ከተደረገ በኋላ የጥናቶቹ ውጤቶችና ሪፖርት የብሔራዊ ም/ቤቱ ሠነዶች ሆነው እንዲመዘገቡ በአብላጫ ድምፅ ተወስኖአል፡፡ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ የጥናትና ምርምር ስራ እንደሚያስፈልግ ተጠቁሟል፡፡ እንዲሁም በጥናቱ ሊካተቱ የሚገባቸው ሐሳቦች ተካተው እንዲዳብሩ ተወስኖአል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በእያንዳንዱ ሠነድ የተጠቆሙ ግኝቶች ላይ በመመርኮዝ ፤ እነሱን በማጠናከርና በማዳበር መርሃ ግብሩንና ዕቅዱን አዘጋጅቶ ለሚቀጥለው ስብሰባ እንዲያቀርብ በመወሰን ምክር ቤቱ ስብሰባውን አጠናቆአል፡፡

ፓርቲያችን አንድነት በምርጫ 2002 ማግስት ባደረጋቸው ተከታታይ ሰብሰባዎች ይህንን የመሰለ ጥልቅ ግምገማ ማድረጉን እጅጉን ይኮራበታል፡፡ ብሔራዊ ምክር ቤቱ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ሁለት ስብሰባዎች ማካሄዱና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በርካታና ተከታታይ ስብሰባዎች በማካሄድ ምክር ቤት ይቅረቡልኝ ያላቸውን ሠነዶች አዘጋጅቶ ማቅረቡ ፓርቲአችን በሥራ ላይ ያለ ዴሞክራቲክ ፓርቲ መሆኑን ያመለክታል፡፡

የፓርቲያችን ሊቀመንበር እስር ላይ ባለችበት ሁኔታ እንዲሁም እንደ መደረክና እንደ ተቀዋሚ ፓርቲ በገዡው ፓርቲና መንግስት በሚደርስብን ጫናና ወከባ ሳንበገር በሥራ ላይ ያለን ቁርጠኛ ዴሞክራቲክ ፓርቲ ሆነን እንቀጥላለን፡፡

ከሁሉ በፊት ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ በሐገራችን ኢትዮጵያ በመንግስትና በገዡው ፓርቲ ኢህአዴግ መካከል ያለው መስመር ከግዜ ወደ ግዜ እየደበዘዘ መሄዱ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በተለይ ከምርጫው ጋር ተያይዞ በከፍተኛ ሁኔታ የተስተዋለ እጀግ አሳሳቢ ክስተት ነው፡፡ በተለይም ነፃ የፍትሕ ሥርዓት ፣ ነፃ የፖሊስና ፀጥታ ተቋማት እና ነፃ የመገናኛ ብዙሐን እጦት በስፋት ተከስቷል፡፡ ኢህአዴግ እነዚህን ተቋማት ከሕግና ከሥርዓት ውጭ በመጠቀም ፓርቲያችንን ለማጥቃት ያለማሰለስ ይሰራ እንደነበር አሁንም እየሰራ መሆኑ እሙን ነው፡፡ በተለያዩ ወቅቶች የፓርቲያችንን ምስል ጥላሸት ለመቀባት በእርሱ ይሁንታና ድጋፍ የሚያቀነባብራቸውን አፍራሽ እንቅስቃሴዎች ተመልሶ ለራሱ ምርጫ ቅስቀሳ ግብአትነት በመጠቀም ሲዘባበትብን መሰንበቱም የቅርብ ግዜ ትውስታ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ የሚያሳየን ነገር ቢኖር የሐገራችን የፖለቲካ ሜዳ ከፍትሐዊነት ይልቅ ከዕለት ወደ ዕለት ገደላ ገደል እየበዛበት መሄዱን ነው፡፡

የአፈሪካ ፀረ ኮሎንያል ትግል ሰንደቅ በመሆን የምትታወሰው አገራችን ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዴሞክራሲ መሳቅያ የሆነውን የግንቦት 2002 ዓ.ም ምርጫ በአካሄደች ማግስት ትናንት ከአስቀያሚው የአፖርታይድ አገዛዝ ነፃ የወጣችው ደቡብ አፍሪካ ለመላ አፍሪካውያን ኩራትና ተስፋ የሆነውን 18ኛውን የዓለም እግር ኳስ ውድድርን እጅግ አሸብራቂ በሆነ ሁኔታ አስተናግዳለች፡፡ ኢትዮጵያውያን ይህንን ጨዋታ ሲከታተሉ ምናለበት የአገራችን የፖለቲካ ሜዳም እንደኳስ ሜዳው የተስተካከለ ቢሆን፣ የኳስ ጨዋታው ሕግጋትና የጨዋታውን ዳኝነት በተመለከቱ ቁጥርም ምናለበት የምርጫው ሕግጋትና የምርጫው አስተዳዳሪዎችና ዳኞች እንደኳስ ጨዋታው ሁሉንም ወገን በእኩል ዓይን የሚመለከቱ ቢሆኑልን ማለታችን አልቀረም፡፡ ይሁንና ጨዋታው መላ አለምን እንዳስደነቀ ሊጠቃለል ጥቂት ሰዓታት ሲቀረው የአፍሪካ አልቃኢዳ ነኝ የሚለው ሌላው የአፍሪካ ሃፍረት የሆነው አልሸባብ በኡጋንዳ ርዕሰ ከተማ ማሳረግያውን ውድድር በቴሌቪዥን ሲከታተሉ በነበሩ ንፁሃን ሰዎች ላይ በፈፀመው አሰቃቂ የሽብር ጥቃት በርካታ ሰዎች ላይ የሞትና የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል፡፡

ከእነዚህ ጉዳተኞች መካከል ኢትዮጵያውያን መኖራቸውንም ለማወቅ ተችሏል፡፡ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ ይህንን የሽብር እርምጃ ያወግዛል፡፡ በዚሁ አጋጣሚ የጥቃቱ ዒላማ ለሆነችው ለዩጋንዳ መንግስትና ለተጎዱ የኡጋንዳ ዜጎች ቤተሰቦች ብርታትንና መፅናናትን ይመኛል፡፡ በዚሁ የሽብር ጥቃት ሰለባ ለሆኑት ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንና ቤተሰቦቻቸው እንዲሁም የውጭ ዜጎችና ቤተሰቦች ሁሉ ብርታቱንና መፅናናቱን ይመኝላቸዋል፡፡

**የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ በዜጐች ያላሰለሰ ጥረት ትግል እውን ይሆናል!**

**ሊቀ መንበራችን ብርቱካን ሚዲቅሳ ጨምሮ ሁሉም የህሊና እስረኞች ይፈቱ!**

**አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ**

**ሐምሌ 16 ቀን 2002 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**